


# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## አገልግሎታችን በፍቅር የተሞላ ይሁን

### በቃል የሚጠና፡- 1ኛ ዮሐ. 4፥7

*“እናንተን በማስታውስበት ጊዜ ሁሉ አምላኬን አመሰግናለሁ.”* **(ፊል. 1፥3)።**

### 1 ጳውሎስ ለሚያገለግላቸው ሰዎች ልዩ ፍቅር ነበረው

*“እናንተን በማስታውስበት ጊዜ ሁሉ አምላኬን አመሰግናለሁ”* የሚለው የሰላምታ ቃል፥ አንድ ከልቡ የሚያገለግል እውነተኛ አገልጋይ፥ ለሚያገለግላቸው ሕዝቦች ያለውን የተቀራረበ ግንኙነትና እንዲሁም ስለ እነርሱ የሚሰማውን የፍቅር ስሜት ጥሩ አድርጎ ይገልጻል። ጳውሎስ ከፊልጵስዩስ አማኞች ጋር የቆየበት ጊዜ ይህን ያህል ረጅም ባይሆንም፥ በጣም ጥሩ የሆነ መቀራረብ ከእነርሱ ጋር ስለነበረው፥ አሁን ርቋቸው በሄደበት፥ ያውም በወህኒ ቤት ተጥሎ ለብቻው በሆነበት ጊዜ ስለነርሱ ሲያስብና ሲጸልይ የሚሰማውን ልዩ የሆነ የደስታ ስሜት ሲገልጽ፥ *“እናንተን በማስታውስበት ጊዜ ሁሉ አምላኬን አመሰግናለሁ”* ይላል።

አገልጋዮች ከሚያገለግሉት ሕዝብ ጋር ባላቸው የተቀራረበ ግንኙነትና ፍቅር ምክንያት ይህን የመሰለ ጥሩ ትዝታ ሲኖራቸው ማየት እንዴት ያስደስታል? ይሁን እንጂ፥ በዘመናችን በአገልጋዮችና በተገልጋዮች መካከል ያለው መቀራረብ ብዙ ጊዜ ይህን አይመስልም። አገልጋዩ፥ አንዳንድ አማኞች የአገልግሎቱ ተባባሪ በመሆን ፈንታ ምን ያህል እንቅፋት እንደሆኑበት፥ እንዲሁም ሕይወቱን ምን ያህል እንዳስመረሩት ያወራል እንጂ፥ ስለ አገለገላቸው ሰዎች የሚያስታውሰው ጥሩ ትዝታ እንዳለው ሲናገር አይሰማም። እንዲሁም ተገልጋዩ የራሱ የሆነ ቅሬታ በአገልጋዩ ላይ አለው። ይህን የመሰለ በደል ቆጠራ ብዙ ጊዜ የሚሰማው ከሁለቱም ወገን ነው። ምክንያቱ ምን ይሆን? የሚያስደንቀው ይህን የመሰለ ቅሬታ ከአገልጋዩም ሆነ ከተገልጋዩ ወገን የሚሰማው በእኛ ዘመን ብቻ ሳይሆን፥ በሐዋርያትም ዘመን የነበረ መሆኑ ነው። ሐዋርያው ዮሐንስ *በዲዮትራፌስ* ላይ የነበረውን ቅሬታ ሲገልጽ እንዲህ ይላል *“ከዚህ በፊት ለቤተ ክርሲቲያን ደብዳቤ ጽፌአለሁ፤ ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን የሚፈልገው ዲዮትራፌስ አሳቤን አልተቀበለም። ስለዚህ ወደ እናንተ ስመጣ ሁሱ እየስደበንና እያዋረደን ያደረገውን ክፉ ሥራ ሁሉ፥ ለሁሉም እናገራለሁ፤ እርሱ የሚያደርገው ይህን ብቻ አይደለም። እርሱ ራሱ ወንድሞችን አይቀበልም። ሊሎችም እንዳይቀበሉአቸው ይከለክላል። ከቤተ ክርስቲያንም ያስወጣቸዋል”* **(3ኛ ዮሐንስ ቁ. 9-10)።**

### 2 ጳውሎስ እግዚአብሔርን ያመሰገነበት ምክንያት ነበረው

ሐዋርያው ጳውሎስ ያለበደሉ እንደ በደለኛ ተቆጥሮ ሮም ወህኒ ቤት ቢጣልም፥ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን እሰማዋለን። እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ምክንያት የሆኑት የፊልጵስዩስ ምዕመናን ነበሩ። እነርሱን ሲያስታውስና እንዲሁም እነርሱን እያሰበ በሚጸልይበት ቁጥር ሁልጊዜ ልዩ የሆነ ደስታ ከውስጡ ይፈልቅ ነበር። በወህኒ ቤት የነበረውን የመከራ ሕይወት ሁሉ ይረሳ ነበር። የወንጌልን ብርሃን ላልሰሙት ለማዳረስ በሚጥርበት ወቅት የፊልጵስዩስ አማኞች ከጎኑ ሆነው ምን ያህል እንዳገዙት፥ ምን ያህል እንደተባበሩት ሲያስታውስ ፍጹም የሆነ ደስታ ይሰማው ነበር። እርሱን ለመርዳት ባደረጉት ጥረት ምክንያት ብዙ ችግር ቢደርስባቸውም፥ ወደ ኋላ ሳያፈገፍጉ እስከ መጨረሻው ድረስ አብረውት መቆማቸው በጣም ያስደንቀው ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ ዛሬ ለእኔና ለእናንተ ደብዳቤ ቢጽፍልን ኖሮ፥ ለፊሊጵስዮስ አማኞች የጻፈውን ዓይነት የምስጋና ደብዳቤ ይጽፍልን ነበር? እኔና እናንተ ወንጌሉን ለማዳረስ የሚታገሉትን እውነተኛ የሆኑ አገልጋዮችን ለመርዳት ከጎናቸው በታማኝነት እስከ መጨረሻው ድረስ የምንቆም መሆናችንን ማየት ይችል ይሆን? ጳውሎስ፥ የፊልጵስዩስ አማኞች ለወንጌሉ ስርጭት ያላቸውን ድርሻ ተረድተው በፈቃዳቸው ይርዱት እንጂ፥ እምነቱንና ተስፋውን የጣለው በእነርሱ ላይ አልነበረም። ጳውሎስ የነበረው ተስፋ በፊልጵስዩስ አማኞች ላይ ሳይሆን፥ ለወንጌሉ ሥርጭት በጠራው ጌታ ላይ ብቻ ነበር። ይህን እውነት ማንኛውም ጌታን “በሙሉ ጊዜ አገለግላለሁ” የሚል አገልጋይ ሊረዳው የሚገባው እውነት ነው። “ደሞዜን ይሰፍሩልኛል” ብሎ ተስፋ ያደረገው ሰዎችን ከሆነ፥ በአገልግሎቱ ከፍተኛ የሆነ ተስፋ መቁረጥና፥ እንዲሁም ትልቅ ችግር እንደሚያጋጥመው አስቀድሞ ማወቅ ይረዳዋል። እነዚህ “ደሞዜን ይቆጥሩልኛል” “ቀለቤን ይሰፍሩልኛል”

ብሎ ያሰባቸው ሰዎች ምናልባት አንድ ቀን እነርሱ እንደሚፈ ልጉት ሆኖ ካልተገኘ፥ እንዲያደርግ ለሚጠይቁት ነገር ሁሉ “እሺ!” ብሎ ካልታዘዘ፥ ስጦታቸውንም ሆነ አሥራታቸውን ለማን እንደሚሰጡ በደንብ ያልገባቸው አማኞች በመሆናቸው፥ ያኮርፉና የገንዘብ እርዳታቸውን በመከልከል ሊቀጡት፥ ወይንም ልክ ሊያገ ቡት መሞከራቸው አይቀርም። ጳውሎስ ከፊልጵስዩስ አማኞች ጋር የነበረው ግንኙነት ግን ከላይ የገለጽነውን ዓይነት አልነበረም። ለእነርሱ ፍቅር ይኑረው እንጂ፥ ተስፋውን የጣለው በእነርሱ ላይ አልነበረም።

## 3 ከዚህ ክፍል የምናገኘው ጠቃሚ ትምህርት

### ሀ ያለፍቅር የምንሰጠው አገልግሎት፥ ፍሬ የለውም

ሐዋርያው ጳውሎስ ለራሱም ሆነ ለፊልጵስዩስ አማ ኞች በድፍረትና እንዲሁም እርግጠኛ ሆኖ መናገር የሚችለው አንድ ነገር ቢኖር፥ በእርሱና በእነርሱ መካከል እውነተኛ የሆነ ፍቅርና መቀራረብ እንዳለ፥ እርሱ ብቻ ሳይሆን እነር ሱም እንደሚወዱት ነው። በአገልጋዩና በተገልጋዩ ምዕመናን መካከል ይህን የመሰለ እውነተኛ የሆነ ፍቅር ስናይ፥ ያንን ዓይነት የፍቅር ስሜት ሊፈጠር የቻለው፥ በሰው ጥረት ሳይ ሆን የእግዚአብሔር እጅ በዚያ ሥፍራ በመሥራቱ ብቻ እንደ ሆነ ልንረዳ ይገባል። የፊልጵስዩስ ምዕመናን ጳውሎስ የወደ ዳቸውን ያህል እነርሱም በጣም ይወዱት ነበር። ፍቅራቸውም ግድ ስላለው፥ ዘወትር ደስ እያለው ይጸልይላቸው ነበር። ለእርሱ ምን ያህል ፍቅር እንደነበራቸውና እንዲሁም ያንን የመሰለ ፍቅር ሊኖራቸው የቻለው፥ በክርስቶስ ፍቅር በመሞ ላታቸው ምክንያት እንደሆነ መረዳት አላቃተውም። የፊልጵ ስዩስ ምዕመናን ፍቅራቸው በቃላት ብቻ ሳይሆን፥ በተግባርም የተገለጸ ነበር።

### ለ ሌሎችን በማገልገል ደስታ ይገኛል

ሐዋርያው ጳውሎስ ሌሎችን በማገልገል ውስጥ ምን ያህል ደስታ ማግኘት እንደሚቻል በተለይ ለፊልጵስዩስ አማ ኞች በጻፈው መልዕክት ላይ በተደጋጋሚ ሲገልጸው እናያለን። ክርስቲያኖች በጎን ነገር ተቀብለን ለራሳችን ብቻ ይዘን አን ቀመጥም። በነጻ እንደተቀበልን በነጻ ለሎች እንሰጣለን። ይህ ንን የምናደርገው ሌሎችን በማገልገል ውስጥ ምን ያህል ትልቅ ደስታ እንደሚገኝ ስለምናውቅ ነው።

### ሐ አገልግሎት የራስን ፍላጎት በማስቀደም የሚሆን አይደለም

ጳውሎስ ለሚያገለግላቸው ሰዎች ራሱን ሙሉ በሙሉ የሰጠ ሰው ነበር። አገልግሎቱ ፍሬያማ ሊሆን የቻለው፥ ስለ ሌሎች ሲል ራሱን መስዋዕት አድርጎ መስጠትን የተለማመደ በመሆኑ ነው። የራሱን ፈቃድና ፍላጎት የሚያስቀድም አገል ጋይ፥ እንደሚገባው አገልግሎቱን መፈጸም አይችልም። አንድ ጊዜ የእግር ኳስ ጨዋታ በጣም የሚወዱ ሁለት ሰዎች ጨዋታ ለማየት ስቴዲየም ገቡ። በጣም ቢርባቸውም ጨዋ ታው እንዳያመልጣቸው ስላልፈለጉ የሚበላም ሆነ የሚጠጣ ነገር ሄደው ገዝተው ለማምጣት ማንኛቸውም ፈቃደኞች አል ነበሩም። እንዳጋጣሚ አጠገባቸው አንድ ልጅ ስለነበረ፥ ሳን ዲዊችና የሚጠጣ ነገር ገዝቶ እንዲያመጣላቸው፥ እንዲሁም ለተላላከበት ለራሱም ገዝቶ እንዲያመጣ ገንዘብ ሰጡት። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ያ ልጅ ሳንድዊቹን እየበላ፥ ለእነርሱ ግን ምንም ሳይዝ ባዶ እጁን መጣ። የተረፈውንም ገንዘብ ሲመልስላቸው፥ “ለእኛ ለምን አልገዛህልንም?” ብለው ጠየ ቁት። ልጁም ለጥያቄያቸው መልስ ሲሰጥ “ሳንድዊቹ ተሸጠ አልቆ የተረፈው አንድ ብቻ ስለነበረ፥ ያንን ለራሴ ገዝቼ መጣሁ” አላቸው። ነገሩ ተረት ይምሰል እንጂ፥ ይህ ልጅ በራሳቸው ላይ ብቻ የሚያተኩሩትን አንዳንድ ሰዎችን ጥሩ አድርጎ ያሳያል። ራሳቸውን የሚያስቀድሙ አንዳንድ አገልጋ ዮች፥ አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙት፥ የሚፈልጉትን ካገኙ ብቻ ነው። ስለራሳቸው ጥቅም እንጂ፥ ስለ ሌሎች ፈጽሞ ግድ የላቸውም። ይሁን እንጂ፥ “ራስ ወዳድነታችን” የዕርዳታ እጆቻችንን ለሌሎች እንዳንዘረጋ ምክንያት ሲሆነን፥ ሌሎችን በማገልገል ውስጥ የሚገኘውን እውነተኛ ደስታ ማጣታችን እንደሆነ እንወቅ። እኔና እናንተ በአገልግሎታችን ውስጥ እውነተኛ ደስታ ለማግኘት ከፈለግን፥ በሕይወታችን ክርስቶስ ንና የምናገለግላቸውን ሰዎች ማስቀደም አለብን። ጳውሎስ የፊልጵስዩስን አማኞች በማገልገሉ ምክንያት ምን ያህል ትልቅ ደስታ እንዳገኘ ይመሰክራል።

---




**የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል በማኅተም አትዝጋው።**

(የዮሐ. ራዕይ 22፥10)




## ሀ የመልእክቱን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት

1. ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች ያቀረበው ሰላምታ ምንን ያሳየናል?

2. ጳውሎስ ከፊልጵስዩስ አማኞች ጋር የነበረው መቀራረብ ምን ዓይነት ነበር?

3. ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ ዲዮትራፌስ ያሰማው ቅሬት ምን ነበር? (3ኛ ዮሐ. 9-10)

4. ጳውሎስ እግዚአብሔርን ያመሰገነበት ምክንያት ምን ነበር?

5. በአገልግሎት ውስጥ በሰው መታመን (መደገፍ) የሚያስከትለው ችግር ምንድነው?

6. በአገልጋዩና በተገልጋዩ መካከል ፍቅር እንዲኖር ምክንያቱ ምን ይሆን?

7. ጳውሎስ አገልግሎቱ ፍሬያማ እንዲሆን ያደረገው ምክንያት ምንድነው?

8. በአገልግሎታችን ደስተኞች ለመሆን ምን ማድረግ ይኖርብን ይሆን?

## ለ በዚህ ክፍል ውስጥ ያገኘነውን ትምሕርት በግል ሕይወታችን ለመለማመድ...

1. ከጌታ የተቀበልኩት አገልግሎቴ ነው የምትሉት ምንድነው?

2. አሁን ባላችሁበት አገልግሎት ውስጥ እግዚአብሔር እንዳስቀመጣችሁ የምታረጋግጡበት ነገር ምን አላችሁ?

3. በአገልግሎታችሁ ውስጥ የሚሰማችሁ ስሜት ምንድነው?

4. ከምታገለግሉት ሕዝብ ጋር ያላችሁ ግንኙነት ምን ዓይነት ነው?


5. በአሁኑ ወቅት በአገልግሎታችሁ ውስጥ የምትከፍሉት ዋጋ ምንድነው?

6. በአገልግሎታችሁ በአሁኑ ወቅት ቅር የምትሰኙበት ነገር ምንድነው?

7. ከምታገለግሉት ሕዝብ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖራችሁ፥ "ማስተካከል አለብኝ" የምትሉት ነገር ምንድነው?

**"...የመዳንን ራስ ቁር የመንፈስን ሰይፍ ያዙ፥ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።..."**

(ኤፌሶን 6፥17)



የትምሕርቱ አዘጋጅ
መለሰ ወጉ

# ስንቅና ትጥቅ

በኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ተዘጋጅቶ፥ በየሁለት ሳምንቱ እየታተመ የሚወጣ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው።

Ethiopian Outreach Ministry
P.O.Box 2241
York, PA 17405
U.S.A.
Phone/Fax: (717)846-2041
E-Mail: eomusa@aol.com
Internet Address:
www.ethiopianoutreach.com

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አድራሻ